አንደኛ ዓመት ቁጥር2

1st Year No.2

ሐረር መጋቢት 5ቀን 1988

Harar March 14. 1996

# የሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት

# ሐረር ነጋሪ ጋዜጣ

# HARAR NEGARI GAZETA

## HARARI PEOPLE NATIONAL REGIONAL STATE



| ያንዱ ዋጋ 1.00 | በሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ምክር ቤት ተጠባባቂነት የወጣ | የፖስታ ሣጥን ቁጥር 272 |
|---|---|---|



ማውጫ


አዋጅ ቁጥር 2/ 1988

የሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት

አስፈጻሚ አካላት ማቋቋሚያ አዋጅ ........................................ ገጽ3


## የሐረሪ ሕ/ብ/ክልላዊ መንግሥት

## አስፈፃሚ አካላትን ለማቋቋምና ሥልጣንና ተግባራቸውን ለመወሰን የወጣ አዋጅ

የሐረሪ ክልል ሕዝብ ራሱን በራሱ የማስተዳደር መብት ተጠቃሚ እንዲሆን በተመቻቸለት ሁኔታ ተጠቅሞ በሽግግሩ ዘመን የክልሉን ሕዝብ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች ደረጃ በደረጃ ለመፍታት የተዋቀሩት የክልሉ መንግሥት አስፈፃሚ አካላት ከተዋቀሩለት ዓላማ አንፃር ያስመዘገቡትን ውጤቶች በመገንዘብ፤

የሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት አስፈፃሚ አካላት ክልሉ ከሚመራበት የአምስት ዓመት መርሀ-ግብር አንፃር አደረጃጀታቸው ለልማትና አስተዳደራዊ ሥራዎች ቀልጣፋነትና ለመርሀ-ግብሩ ግብመምታት እንዲያግዝ ሆኖ መዋቀር እንዳለባቸው የታመነበት በመሆኑ፤

በሁሉም መስኮች ቅንጅታዊ አሠራር ርን ለማጎልበት ሀ ብትንና የሰው ኃይልን በአግባቡ ለመጠቀምና አስተዳደራ ዊ ወጪን በመቀነስ አብዛኛውን የክልሉን በጀት በልማት ሥራ ላይ ለማዋል ይረዳ ዘንድ የክልሉን መንግ ሥት አስፈፃሚ አካላት በአዲስ መልክ በማቋቋም እና ሥል ጣንና ተግባራቸውን በህግ መወሰን አስፈላጊ በመሆኑ፤

በሐረሪ ሕ/ብ/ክ/መ ም/ቤት የክልሉ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 26/1/ሀ መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

## ምእራፍ አንድ

## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

### 1. አጭር ርእስ

ይህ አዋጅ "በሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የአስፈፃሚ አካላት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 2/1988" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

### 2. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፤

1. "ክልል ማለት" በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግሥት በአንቀጽ 47 መሠረት የተቋቋመውን የሐረሪ ህዝብ ክልል ነው።

2. "ምክር ቤት" ማለት የሐረሪ ህዝብ ክልል ምክር ቤት ማለት ነው።

3. "የክልሉ መንግሥት" ማለት የሐረሪ ህዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ማለት ነው።

4. "አስፈፃሚ አካላት" ማለት የክልሉን ኢኮኖሚያዊ ማህበራዊ እና ፖለቲካዊ ፖሊሲዎችን ለማስፈፀም በዚህ አዋጅ የተቋቋሙት ቢሮዎችና ጽ/ቤቶች ናቸው።

5. "የገበሬ የህብረት ሥራ ማህበር" ማለት በሐረሪ ሕዝብ ክልል በገጠር ውስጥ አርሶ አደሮች በፍላጎታቸው የሚያቋቁሙት የአገልግሎት፣ የአምራቾችና ሁለገብ የገበሬዎች የህብረት ሥራ ማህበር ነው።

3. <u>መቋቋም፣</u>

በሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት በዚህ አዋጅ የተደነገገውን ተግባር ለማከናወን ኃላፊነት የተጣለባቸው የሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የአስፈፃሚ አካላት የሆኑት ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ቢሮዎች በዚህ አዋጅ ተቋቁመዋል፣

1. የግብርና ልማት ቢሮ፣

2. የሥራና ከተማ ልማት ቢሮ፣

3. የትራንስፖርት፣ ንግድ፣ ኢንዱስትሪና ቱሪዝም ቢሮ፣

4. የውሃ ሀብት፣ የማዕድንና ኢነርጂ ልማት ቢሮ፣

5. የፕላንና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ፣

6. የፋይናንስ ቢሮ፣

7. የጤና ቢሮ፣

8. የአደጋ መከላከል፣ የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮ፣

9. ሲቪል ሰርቪስ ቢሮ

10. የፍትህ ቢሮ እና

11. የባህልና ስፖርት ቢሮ።

4. <u>የጽህፈት ቤቶች ስለመቋቋም</u>

በሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት በዚህ አዋጅ የተደነገገውን ተግባር የማከናወን ኃላፊነት የተጣለባቸው የሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የአስፈፃሚ አካላት የሆኑ ከዚህ በታች የተዘረዘሩ ጽህፈት ቤቶች በዚህ አዋጅ ተቋቁመዋል።

1. የቤቶች ጉዳይ ዘርፍ፣

2. የኢንቬስትመንት ጽ/ቤት እና

3. የሥነ-ሕዝብ ጽ/ቤት።

<u>ምዕራፍ ሁለት</u>

<u>የሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የቢሮዎች ሥልጣንና ተግባር</u>

<u>ክፍል አንድ</u>

<u>የቢሮዎችና የቢሮ ኃላፊዎች ሥልጣንና ተግባር</u>

5. <u>የወል ሥልጣንና ተግባር</u>

በዚህ አዋጅ የተቋቋሙ የሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ቢሮዎች በዚህ አዋጅ ውስጥ ለእያንዳንዳቸው የተሰጣቸው ዝርዝር ሥልጣንና ተግባር እንደተጠበቀ ሆኖ የሚከተሉት የወል ሥልጣንና ተግባር ይኖራቸዋል።

1. እያንዳንዱ ቢሮ በሥራው መስክ፦

ሀ. የክልሉን የአጭር፣ የመካከለኛና የረዥም ጊዜ መርሃ-ግብር መሠረት በማድረግ እቅድና በጀት በማዘጋጀት ለበላይ በማቅረብ እንዲፀድቅ የማድረግ፣ ሲፀድቅም በሥራ ላይ የማዋል፣

ለ. የፌዴራል መንግሥትና የክልሉ መንግሥት ህጎች፣ ደንቦችና መመሪያዎች በክልሉ ውስጥ በሥራ ላይ መዋላቸውን የማረጋገጥ፣

ሐ. አስፈላጊ ሆኖ በሚገኝበት ጊዜ ፖሊሲዎች፣ ሕጎችና ደንቦችን በማመንጨት እንዲጸድቁ ለክልሉ ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ የማቅረብ፣ ሲጸድቅም በሥራ ላይ የማዋል፣

መቆየናትና የምርምር ሥራዎችን የማከናወን፣ የስታስቲክስ መረጃዎችን በማሰባሰብና በማቀነባበር ለሚመለከታቸው አካላት የማስተላለፍ፣

ሠ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ተገቢውን የሥራ ግንኙነት የማድረግ፣

ረ ሕግ በሚያዘው መሠረት ውሎችን የመዋዋል፣ በፍርድ ቤት የመክሰስና የመከሰስ፣

2. እያንዳንዱ ቢሮ በሕግ የተሰጠውን ተግባር የማስፈፀም መብት ለማጎልበት ስልቶችን በመቀየስ፣ የአፈፃፀም መመሪያዎችን የማውጣት፣ እንዲሁም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመመካከር የክልሉ መንግሥት በሚያደራጀው የመስተዳደር እርከኖች መሠረት መዋቅሩን የመዘርጋት፣

3 እያንዳንዱ ቢሮ በዚህ አዋጅ የተደነገጉትን እና ባልተሻሩ ሕጎች የተሰጡትን ሥልጣንና ተግባር የማከናወን፣

4. እያንዳንዱ ቢሮ ለክልሉ ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ የመሥሪያ ቤቱን የሥራ እንቅስቃሴ በየሦስት ወሩ በግባ ያቀርባል።

6. የቢሮ ኃላፊዎች ተጠሪነት፣

እያንዳንዱ የቢሮ ኃላፊ ተጠሪነቱ ለክልሉ ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴና ለክልሉ ርእሰ መስተዳድር ይሆናል።

7. የቢሮ ኃላፊዎች ሥልጣንና ተግባር፣

የሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የቢሮ ኃላፊዎች በዚህ አዋጅ ለየቢሮዎቹ ከተሰጠው ሥልጣንና ተግባር በተጨማሪ የሚከተለው ሥልጣንና ተግባር ይኖራቸዋል።

1. ቢሮዎቻቸውን በበላይነት ይመራሉ፣ ይጠነክላሉ፣

2. ለቢሮዎቻቸው የተፈቀደውን በጀት በፋይናንስ ደንብና መመሪያ መሠረት ያስተዳድራሉ፣

3 በዚህ አዋጅ መሠረት ለቢሮው የተሰጠውን ሥልጣንና ኃላፊነት ያከናውናሉ።

## ክፍል ሁለት

## የሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የቢሮዎች ዝርዝር ሥልጣንና ተግባር

### 8. የሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የግብርና ልማት ቢሮ ሥልጣንና ተግባር

የሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የግብርና ልማት ቢሮ የሚከተለው ሥልጣንና ተግባር ይኖረዋል፣

1. በሀገሪቱ ፖሊሲና ህግ መሠረት የክልሉን የገጠር መሬት አጠቃቀም፣ የደንና ዱር አራዊት ሀይወት እና የሀብት ጥበቃና አጠቃቀም ደንቦች ያዘጋጃል፣ ሲፈቀድም በሥራ ላይ ያውላል፣

2. ለገበሬዎች የሚሰጡ የግብርና ኤክስቴንሽን አግልግሎቶች በክልሉ እንዲስፋፉ ያበረታታል፣ ድጋፍ ይሰጣል፣

3. አግባብ ካላቸው አካላት ጋር በመተባበር የግብርና ምርት ማሳደጊያዎች፣ የእርሻ መሣሪያዎች አገልግሎት፣ የፀረ-ሰብል ተባይ መከላከያ ኬሚካሎች፣ የእንስሳት መድኃኒትና የብድር አገልግሎቶች ለክልሉ ገበሬዎች የሚቀርቡበትን ሁኔታ ያመቻቻል፣

4. የግብርና ልማትን ለማፋጠንና የገጠር ቴክኖሎጂን ለማሻሻል ከሚመለከታቸው የምርምርና የማሰልጠኛ ማዕከሎች ጋር በትብብር ይሰራል፣ አስፈላጊውንም ድጋፍ ይሰጣል፣

5. የገበሬዎች የህብረት ሥራ ማህበር በክልሉ እንዲደራጅና እንዲስፋፋ ያበረታታል፣ ተገቢውን ድጋፍ ይሰጣል፣

6. የግብርና ኢንቬስትመንት እንዲስፋፋ ያበረታታል፣ እንዲሁም በግብርና ዘርፍ ለሚሰማሩ የሀገር ውስጥ ባለሀብቶች የግብርና ሥራ ፍቃድ ይሰጣል፣ ይቆጣጠራል፣

7. ተዛማጅ የሰብልና የእንስሳት በሽታ እንዲሁም የፀረ ሰብል ተባይ በክልሉ ሲከሰት አስቸኳይ የመከላከል ዕቅድ በማውጣት በክልሉ የሚገኙ መንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ ተቋሞችንና የክልሉን ህብረተሰብ በማስተባበር በባህላዊና ዘመናዊ ሕክምና ይከላከላል፣ በቁጥጥር ሥር ያውላል፣

8. የክልሉ የደን ሀብት ልማት እንዲስፋፋ ያበረታታል፣ ብቁ የሆነ የደን ዛፍ ችግኝና

የቴክኒክ አገልግሎት እንዲዳረስ ጥረት ያደርጋል፤

9. የተፈጥሮ ኃብት መመናመን በአካባቢ ላይ የሚያደርሰውን ጉዳት ለመቆጣጠር፣ የውኃ፣ የአፈርና የአየር ብክላን ለመከላከል የወጡትን መመሪያዎች ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር በክልሉ ውስጥ መከበራቸውን ይቆጣጠራል፤ እንዲሁም የአፈርና ውኃ ጥበቃ ሥራ ሥልት እየቀየሰ በተግባር ላይ ያውላል፤

10. ወደ ክልሉ በሚገቡ ወይም ከክልሉ በሚወጡ እፅዋት፣ አዝርእት፣ እንስሳትና የእንስሳት ተዋጽኦ ላይ ተገቢውን የኳራንቲን ቁጥጥር እንዲካሄድ ያደርጋል፤

11. በክልሉ ውስጥ በጥቅም ላይ የሚውሉ የእንስሳት መድሃኒትና ፀረ-ተባይ ኬሚካሎችን ይመዘግባል፤ በአግባቡ ስለመያዛቸውም ይቆጣጠራል፤

12. በክልሉ ውስጥ የሚገኙ ለአደን የተከለከሉ ቦታዎችንና ጥብቅ ደኖችን ያስተዳድራል፤

13. የሚትሮሎጂ መረጃዎችን በመሰብሰብ ለሚመለከታቸው አካላት አስፈላጊውን ትብብር ያደርጋል።

## 9. የሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የሥራና ከተማ ልማት ቢሮ ሥልጣንና ተግባር

የሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የሥራና ከተማ ልማት ቢሮ የሚከተሰው ሥልጣንና ተግባር ይኖረዋል፤

1. የህንፃ ኮድ፣ የዲዛይንና የኮንስትራክሽን ሥራ ደረጃዎች በክልሉ ውስጥ መከበራቸውን ያረጋግጣል፤

2. በክልሉ መንግሥት በጀት ለሚሠሩ የመንግሥት ኮንስትራክሽኖች የሚያስፈልጉ ዲዛይኖችና የኮንስትራክሽን ሥራ ውሎች ሕግ በሚያዘው መሠረት እንዲዘጋጁ ያደርጋል፤

3. በክልሉ መንግሥት በጀት የሚሠራ የኮንስትራክሽን ሥራ በተደረገው ውል መሠረት የጥራት ደረጃው የጊዜና የዋጋ ገደቦች ተጥብቀው መሠራቱን ለማረጋገጥ የሚያስችል ቁጥጥር እንዲኖር ያደርጋል፤ በበላይነት ይቆጣጠራል፤

4. በክልሉ ከተሞች ውስጥ ለሚካሄድ ኢንቬስትመንት በከተማ ቦታና የኮንስትራክሽን ሥራዎች ለሚደረገው እንቅስቃሴ አስፈላጊውን ትብብር ያደርጋል፤ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፤

5. ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር በከተሞች ውስጥ በኢንቬስትመንት ለሚካሄደው የግል የኪራይ ቤቶች ግንባታ የሥራ ፍቃድ ይሰጣል፤

6. በክልሉ መንግሥት ባለቤትነት ሥር የሚገኙ የከተማ ቤቶችና ሕንፃዎችን በሚመለከት ቴክኒካዊ ድጋፍ ይሰጣል፤ ያስተዳድራል፤

7. ለከተሞች ፕላን ዝግጅት የሚረዱ ጥናቶችን ያካሄዳል፤ ከሚመለከታቸው የፌዴራል መንግሥት አካላት ጋር ለከተሞች ፕላን ዝግጅት አስፈላጊውን ትብብር ያደርጋል፤ የከተሞችን ፕላን ለማስፈፀም የሚያስፈልጉ ዝርዝር ፕላኖች እንዲዘጋጁ ያደርጋል፤ አፈፃፀማቸውን ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል፤ እንዲሁም የከተሞችን ደረጃ በየጊዜው እያጠና ይወስናል፤

8. የከተማ ነዋሪ ሕዝብ ከአቅሙ ጋር የተመጣጠነ ቤቶችን ሰርቶ እንዲጠቀም ሁኔታዎችን ያመቻቻል፤

9. የመኖሪያ ቤት ህብረት ሥራ ማህበራት እንዲቋቋሙ ያበረታታል፤ ድጋፍ የሚያገኙበትን መንገድ ይቀይሳል፤

10. በክልሉ ከተሞች ውስጥ የመኖሪያ ቤት ችግርን ለማቃለል የቁጠባ ቤቶች እንዲሰሩና እንዲከራዩ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፤ ያበረታታል፤

11. በክልሉ የሚገኙ ማዘጋጃ ቤቶችን በጀት፣ እቅድና የከተማ ፕላን አዘገጃጀትና አፈፃፀም፣ የሰው ኃይል ስምሪት፣ የአስተዳደርና የገቢ አሰባሰብን ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል፤

12. ለሀገር ውስጥ ሥራ ተቋራጮችና የኮንስትራክሽን አማካሪዎች ፍቃድ ይሰጣል፤ ይቆጣጠራል፤

13. የኮንስትራክሽን፣ የከተማ ልማትና ቤት ፖሊሲዎችን በክልሉ ውስጥ ተግባራዊ ያደርጋል፤

14. በክልሉ መንግሥት በጀት የሚሠሩ የመንግሥት ኮንስትራክሽኖች እንዲሠሩ፣ እንዲሻሻሉና እንዲጠገኑ ያደርጋል፤

15. በክልሉ የሚቋቋሙት የኮንስትራክሽንና የሙያ ማህበራትን ይመዘግባል።

## 10. የሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የትራንስፖርት፣ ንግድ፣ ኢንዱስትሪና ቱሪዝም ቢሮ ሥልጣንና ተግባር

የሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የትራንስፖርት፣ ንግድ፣ የኢንዱስትሪና ቱሪዝም ቢሮ የሚከተለው ሥልጣንና ተግባር ይኖረዋል።

1. የሀገሪቱን የትራንስፖርት፣ ንግድ፣ ኢንዱስትሪና ቱሪዝም ልማት ፖሊሲ መሠረት ያደረገ በክልሉ የትራንስፖርት፣ ንግድ፣ ኢንዱስትሪና እደ-ጥበብ እንዲስፋፉ ያበረታታል፣ እንዲሁም የቴክኒክ የምክርና ሌሎች አስፈላጊ የሆኑ አገልግሎቶችን ይሰጣል።

2. የክልሉን የትራንስፖርት እና የንግድ እንቅስቃሴ በሀገሪቱ ህግና ፖሊሲ መሠረት መካሄዱን ይቆጣጠራል፣ እንዲሁም ህጋዊ ያልሆኑ የማምረት አገልግሎት የመስጠትና የንግድ ልውውጥ ሥራ እንዳይካሄድ ያደርጋል።

3. በኢንቨስትመንት ፖሊሲና ህግ መሠረት ሊጠኑና በሥራ ላይ ሊውሉ የሚገባቸውን የኢንዱስትሪ ፕሮጀክት ሃሳቦችን ለሚመለከተው ለፌዴራሉ መንግሥት መ/ቤት ያስተላልፋል፣ እንዲሁም ሌሎችም የኢንዱስትሪ ፕሮጀክት ሃሳቦች በክልል ደረጃ እንዲጠኑና በሥራ ላይ እንዲውሉ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፣

በክልሉ ውስጥ የሚገኙ ተሽከርካሪዎችን ይመዘግባል፣ የቴክኒክ ምርመራ ያደርጋል፣ ተሽከርካሪዎችን የመንዳት ፍቃድ ይሰጣል፣ ሕግ በሚያዘው መሠረት ለተሽከርካሪ ባለቤቶች የባለቤትነት ማረጋገጫ እና ለተሽከርካሪዎች ሰሌዳ ይሰጣል፣ ለሚሰጠው አገልግሎት አግባብ ያለው ክፍያ ያስከፍላል፣ የተገኘውም ገቢ በአግባቡ መያዙን ያረጋግጣል።

5. በክልሉ ውስጥ ለሚቋቋሙ የተሽከርካሪ መጠገኛና ማደሻ ጋራዥና ባለሞተር ተሽከርካሪ መንዳት ለሚያስተምሩ ሰዎችና ድርጅቶች ፍቃድ ይሰጣል፣ ይቆጣጠራል።

6. ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር በክልሉ የመገናኛ አግልግሎት የሚስፋፋበትን ሁኔታ አጥንቶ በሥራ ላይ የሚውልበትን ሁኔታ ያመቻቻል።

7. በክልሉ ውስጥ በመሠረታዊ የንግድ ዕቃዎችና አገልግሎቶች ስርጭት አግባብነት ባለው አካል የተወሰነው የዋጋ ተመንና የጥራት ደረጃ መከበሩን ይቆጣጠራል።

8. የክልሉ የኢንዱስትሪ፣ የእርሻና የሌሎች የምርት ውጤቶችን ለማስተዋወቅ ኤግዚቢሽን እንዲዘጋጅ ያደርጋል፣ በሌሎች ክልሎች በሚዘጋጀው ተመሳሳይ ኤግዚቢሽኖች ይሳተፋል።

9. ክልሉ ከሌሎች ክልሎች ጋር የሚያደረገው የንግድ ልውውጥ የሚስፋፋበትና የሚዳብርበትን ሁኔታ ያመቻቻል።

10. በክልሉ ውስጥ በትራንስፖርት፣ በንግድና በኢንዱስትሪ ሥራ ለሚሠማሩ ለአገር ውስጥ ባለሀብቶች ፍቃድ ይሰጣል፣ ይቆጣጠራል፣ እንዲሁም ተገቢውን የአገልግሎት ገቢ ይሰበስባል።

11. ለዕደ-ጥበባት፣ ለነጆ ኢንዱስትሪዎችና ለአነስተኛ ኢንዱስትሪዎች የኤክስቴንሽን አገልግሎት ይሰጣል፣ እንዲሁም እንደ አስፈላጊነቱ የዕደ-ጥበባትና ነጆ ኢንዱስትሪዎች የሙያ ማሻሻያ ማዕከሎች እንዲቋቋሙ ያደርጋል።

12. የክልሉን የንግድ መዝገብ ያቋቁማል፣ ያስተዳድራል።

13. የአነስተኛ ኢንዱስትሪ፣ የዕደ-ጥበባትና የሸማቾች የህብረት ሥራ ማህበራት እንዲቋቋሙ ያበረታታል፣ አስፈላጊውን ድጋፍ ይሰጣል።

14. በክልሉ የንግድ ምክር ቤቶች እንዲቋቋሙ ያበረታታል፣ ድጋፍ ይሰጣል።

15. ስለ ክልሉ የንግድ ሥራ እንቅስቃሴና የትራንስፖርትና የኢንዱስትሪ ልማት መረጃዎችን ያሰባስባል፣ ያጠናቅራል፣ ለሚመለከታቸው አካላት ያስተላልፋል።

16. በሀገሪቱ የቱሪዝም ፖሊሲ መሠረት በክልሉ የቱሪስት አገልግሎቶች እንዲስፋፉ ያበረታታል።

17. የክልሉ የቱሪስት መስህቦች በጎብኚዎች እንዲታወቁ ያደርጋል።

18. አግባብ ካላቸው የክልሉ የመንግሥት አካላት ጋር በመተባበር የክልሉን ቱሪስት መስህቦች ይመዘግባል፣ እንዲደራጁ፣ እንዲስፋፉና እንዲጠበቁ ያደርጋል።

19. በክልሉ በሀገር ውስጥ ባለሀብቶች ከሆቴል አገልግሎት ውጭ ለሚካሄዱ የቱሪስት አግልግ

ሎት ሰጭ የዕደ-ጥበባት ተቋሞች ፍቃድ ይሰጣል፤ ይቆጣጠራል፤

20. የቱሪስት አገልግሎት ሰጭ ተቋማት የተወሰነላቸውን ደረጃ መጠበቃቸውን ያረጋግጣል፤ ይቆጣጠራል፤

21.የክልሉን የቱሪዝም እድገት ለማፋጠን የሚረዱ ጥናቶች ያካሄዳል፤

22. የክልሉን የቱሪዝም መረጃዎች ያሰባስባል፤ ያዘጋጃል፤ ያሰራጫል፤

23.ቱሪዝም ነክ በሆኑ ጉዳዮች አግባብ ያላቸውን አካላት ያስተባብራል፤

24. የሕዝብ ትራንስፖርት ማመላለሻ ማህበራት የሚያወጡትን የትራንስፖርት ስምሪት ፕሮግራም በመመርመር ያጸድቃል፤ ባፀደቀው ፕሮግራም መሠረት የትራንስፖርት ስምሪት መከናወኑን ይቆጣጠራል፤

25.በክልሉ ውስጥ የሚገኙትን የትራንስፖርት መናኸሪያዎችን ይመራል፤ ይደራጃል፤ ይቆጣጠራል እንደ አስፈላጊነቱ አዲስ የትራንስፖርት መናኸሪያዎችን ያቋቁማል።

## 11. የሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የውኃ ሀብት የማዕድንና ኢነርጂ ልማት ቢሮ ሥልጣንና ተግባር

የሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የውኃ ሀብት የማዕድንና ኢነርጂ ልማት ቢሮ የሚከተለው ሥልጣንና ተግባር ይኖረዋል፤

1.ስለ ውኃ ሀብትና ማዕድን ጥበቃ አጠቃቀም የወጡ ህጎች፤ ደንቦችና መመሪያዎች በክልሉ ውስጥ መከበራቸውን ያረጋግጣል፤

2. በክልሉ የሚገኙ ሸለቆዎችን፤ የተፈጥሮ ሀብት ክምችትና ሥርጭትን ያጠናል፤ መረጃዎች ይሰበስባል፤ ይመዘግባል፤ እንዲሁም ከሚመለከታቸው ሌሎች አካላት ጋር በመተባበር በሚካሄዱት ጥናቶች ላይ ይሳተፋል፤

3. የክልሉ የውኃ ሀብት ለልዩ ልዩ ግልጋሎት ሚዛናዊ በሆነ መንገድ መከፋፈሉንና በጥቅም ላይ መዋሉን ይቆጣጠራል፤

4. የክልሉን የውኃ ሀብት በሚመለከት ግድቦችና ሌሎች ሥራዎችን ለመሥራትና በጥቅም ላይ ለማዋል ለሚፈልጉ ኢንቨስተሮች ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ፍቃድ ይሰጣል፤ ይቆጣጠራል፤

5.በክልሉ የመጠጥ ውኃ ሥራን ለማስፋፋት በሚደረገው ጥረት ዲዛይኖች፤ ኮንስትራክሽኖች፤ እንዲሁም በሥራ ላይ ለነበሩ የኦፕሬሽንና የጥገና ሥራ ያካሂዳል፤

6. የክልሉ ውኃ ሀብትን ታሪፍ በተመለከተ ጥናቶች ያካሂዳል፤ ሲፈቀድ በሥራ ላይ መዋሉን ይቆጣጠራል፤ ከሚመለከተው አካል ጋር በመተባበር የውኃ ክፍያ ይሰበስባል፤

7. ለልዩ ልዩ አገልግሎቶች የሚውል ው[illegible] የተወሰነውን የጥራት ደረጃ የጠበቀ መሆኑን፤ እንዲሁም ለልዩ ልዩ ፍሳሾች የተወሰነው የጤናማነት ደረጃ በክልሉ ውስጥ በሥራ ላይ መዋሉን ይቆጣጠራል፤

8. የሜትሮሎጂና የኃይድሮሎጂ መረጃዎችን በመሰብሰብ ረገድ ከሚመለከተው አካል ጋር አስፈላጊውን ትብብር ያደርጋል፤

9. በክልሉ ውስጥ የማዕድንና ኢነርጂ ልማት እንዲስፋፋ ያበረታታል፤

10. በውኃና በማዕድን ሀብት አጠባበቅ ረገድ ከሚመለከታቸው የፌዴራል መንግሥት አካላት ጋር ይተባበራል፤ እንዲሁም በክልሉ ውስጥ ለሚካሄደው የውኃ፤ የማዕድንና ኢነርጂ ልማት ሥራዎች አስፈላጊውን ድጋፍ ይሰጣል፤

11. በክልሉ ውስጥ የኤሌክትሪክ ኃይ[illegible] አቅርቦትን ለማዳረስ በነዳጅ ኃይል የሚሠሩ አነስተኛ የውኃ ኃይል ኤሌክትሪክ ማመንጫ ጣቢያዎች ስለሚቋቋሙበት ሁኔታ ያጠናል፤ ሲፈቀድም በሥራ ላይ እንዲውል ያደርጋል፤ እንዲሁም አነስተኛ የኤሌክትሪክ ኃይል የማመንጨትና የማሰራጨት ፍቃድ ይሰጣል፤ ይቆጣጠራል፤

12. ባህላዊ የማዕድን ማምረቻ ሥራዎችን ያበረታታል፤ በዚህም መስክ የሥራ ፍቃድ ይሰጣል፤ይቆጣጠራል እንዲሁም ከነዚህና ከሌሎች የሥራ መስኮች የሚገኘውን ገቢ ይሰበስባል፤ በአግባቡ መያዙንም ያረጋግጣል፤

13.በክልሉ የመስኖ ልማት ሥራዎችን ያካሂዳል፤

14.የውኃ፤ የማዕድንና ኢነርጂ ሀብትን የሚመለከቱ ጥናቶች ያካሂዳል፤ እንዲጠና ያደርጋል፤ መረጃዎችን ይሰበስባል፤ ያደራጃል።

## 12.የሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የፕላንና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ ሥልጣንና ተግባራት

የሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የፕላንና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ የሚከተለው ሥልጣንና ተግባር ይኖረዋል፤

1. በአገሪቱ አጠቃላይ የልማት ፖሊሲና ስትራቴጂ መሠረት በክልሉ መንግሥት በሥራ ላይ የሚውሉ የረጅም፣ የመካከለኛና የአጭር ጊ የልማት ዕቅድ ያዘጋጃል፤ ሲፈቀድም በሥራ ላይ መዋሉን ይከታተላል፤

2.ከሚመለከታቸው የክልሉ መንግሥት አካላት ጋር በመተባበር በክልሉ ውስጥ በረዥም፣ በመካከለኛና በአጭር ጊዜ ዕቅዶች ውስጥ የሚካተቱ ፕሮጀክቶች እንዲጠኑና እንዲዘጋጁ ያደርጋል፤ ይገመግማል፤

3. በክልሉ የመንግሥት አካላት እየተዘጋጁ የሚቀርቡለትን አመታዊ የልማት ዕቅዶችና ለፕሮጀክቶች የሚያስፈልገው የካፒታል በጀት ጥያቄዎችን መርምሮ የተጠቃለለ የልማት ዕቅድና የካፒታል በጀት አዘጋጅቶ ለክልሉ ፋይናንስ ቢሮ ያስተላልፋል፤

4.በሀገሪቱ የኢኮኖሚ ፖሊሲ መሠረት የክልሉ የግል ክፍለ-ኢኮኖሚ ተሳትፎ እንዲበረታታ ድጋፍ ሰጭ የሆኑ አመልካች ዕቅድ ያዘጋጃል፤

5.የክልሉን የረዥም፣ የመካከለኛና የአጭር ጊዜ የልማት ዕቅድለማዘጋጀትየሚረዱ የክልሉን የምርት ስፔሻላይዜሽንና የተለያዩ የልማት አቅም ላይ ጥናትና ምርምር ያካሂዳል፤

6.ከኢኮኖሚ ልማትና ትብብር ሚ/ር ለክልሉ የፕላን አዘገጃጀትና አቀራረብ የሚተላለፉትን መመሪያዎች ለክልሉ አመቺ በሚሆን መልኩ ተዘጋጅቶ ከማብራሪያ ጋር ለክልሉ የመንግሥት አካላት በወቅቱ እንዲደርሱ ያደርጋል፤

7.የክልሉን የተፈጥሮ ኃብት፣ የምርት፣ የህዝብ፣ የሳይንስና ቴክኖሎጂ ስርጭትና የአገልግሎት መረጃዎችን ያሰባስባል፤ ያጠናቅራል፤ ለሚመለከታቸው አካላት ያስተላልፋል፤

8. የየሴክተሩን የዕቅድ አፈፃፀም እየገመገመ የተቀናበረ ሪፖርት በየሶስት ወሩ ለክልሉ መንግሥት የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ያቀርባል፤

9. ለክልሉ ልማትና እድገት የሚያስፈልጉ የቅየሳ፣ የካርታና የጂኦግራፊ ጥናት ሥራዎች እንዲከናወኑ ያደርጋል።

## 13. የሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የፋይናንስ ቢሮ ሥልጣንና ተግባር

የሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የፋይናንስ ቢሮ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖረዋል፤

1. የክልሉ መንግሥት አካላት የሀገሪቱን ፋይናንስ ፖሊሲዎች፣ ህጎች፣ ደንቦችና መመሪያዎች ተከትለው መሥራታቸውን ይቆጣጠራል፤

2. በክልሉ የመንግሥት አካላት እየተዘጋጁ የሚቀርቡለትን የበጀት ጥያቄዎችና ከክልሉ የፕላንና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ እየተዘጋጁ የሚተላለፉለትን የመደበኛና የካፒታል በጀት መርምሮ የክልሉን ዓመታዊ በጀት አስተያየቱን በማከል ለክልሉ መንግሥት የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ያቀርባል፣ የተፈቀደውን በጀት ያስተዳድራል፤

3. የክልሉ መንግሥት የፋይናንስ ክንውንና የገንዘብ ይዞታን የሚያሳይ ጠቅላላ መግለጫ በየወቅቱ ለክልሉ የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ያቀርባል፣ እንዲሁም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ተጨማሪ በጀት አዘጋጅቶ ያቀርባል፤

4. አግባብ ባለው ህግ መሠረት ከማናቸውም የገቢ ምንጭ ግብርና ታክስ ይወስናል፣ ይሰበስባል፣ የተሰበሰበውም ገቢ በአግባቡ መያዙን ያረጋግጣል፣ እንዲሁም የክልሉ መንግሥትየገቢ መሠረት የሚስፋፋበትንና ፍትሀዊ የገቢ አሰባሰብ ሥርዓት የሚኖርበትን ሁኔታ ያመቻቻል፤

5.የክልል መንግሥቱን የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት ይመሰርታል፤ በክልሉ የመንግሥት አካላት በሥራ ላይ መዋሉን ይቆጣጠራል፣ ሂሳቦቹን ይመረምራል፤

6. የክልሉ መንግሥት ከሀገር ውስጥ የብድር ምንጮች የሚያገኛቸውን ብድሮች በክልሉ መንግሥት ስም ይፈራረማል፤ የተገኘውን ብድር እየተቆጣጠረ ያስተዳድራል፤

7. የክልሉን መንግሥት የንብረትና አገልግሎት ግዥና አጠቃቀም መመሪያ ያዘጋጃል፣ በሥራ ላይ መዋሉን ይቆጣጠራል፣

8. የክልሉ የመንግሥት አካላት ሥር የማይተዳደር ወይም ጥቅም ላይ ያልዋለ የክልሉ መንግሥት ንብረትን ኃላፊ ሆኖ ያስተዳድራል፣

9. የክልሉ መንግሥት አክሲዮኖችን እንዲሁም የሚተላለፉና የማይተላለፉ የክልሉ መንግሥት የገንዘብ ሰነዶችና ሌሎች ተመሳሳይ ተቀማጭ የገንዘብ ሀብቶችን ይይዛል፣ ይጠብቃል።

## 14. የሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የትምህርት ቢሮ ሥልጣንና ተግባር

የሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የትምህርት ቢሮ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖረዋል፤

1. በክልል አቀፍ ደረጃ ትምህርትን ለማስፋፋት የሚያስችሉ ሥልቶችን ይቀይሳል፣ ለተግባራዊነታቸውም ሁኔታዎችን ያመቻቻል፣

2. በሀገሪቱ የትምህርት ፖሊሲ መሠረት የክልሉን የትምህርት ዕቅድና ፕሮግራም ያዘጋጃል፣ ሲፈቀድም በስራ ላይ ያውላል፣

3. በክልሉ ለትምህርት የደረሱ ሁሉ የመማር እድል የሚያገኙበትን ስልት ይቀይሳል፣ መሠረተ ትምህርት ለሁሉም እንዲዳረስ ያደርጋል፣

4. የክልሉ የትምህርት ጥራት በሀገር አቀፍ የተወሰነውን ስታንዳርድ የጠበቀ መሆኑን ያረጋግጣል፣

5. የሀገሪቱን የትምህርት ፖሊሲና ስታንዳርድ ተከትሎ የክልሉንና የአካባቢውን ሁኔታ በማገናዘብ የክልሉን የአፀደ ህፃናትና የጎልማሶች የአንደኛና መለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶችና የመምህራን ማሰልጠኛ ተቋማትን ሥርዓተ ትምህርት ያዘጋጃል፣ በማናቸውም ደረጃ የሚዘጋጀው ሥርዓተ ትምህርት ከሃይማኖት፣ ከፖለቲካ፣ አመለካከትና ከባህላዊ ተፅእኖዎች ነፃ መሆኑን ያረጋግጣል፣

6. በክልሉ በየደረጃው ለማስተማር ብቁ የሚያደርጉ መመዘኛዎች መሟላታቸውን ያረጋግጣል፣ መምህራንና የትምህርት ባለሙያዎችን ያሰለጥናል፣

7. በሀገር አቀፍ ደረጃ ተዘጋጅተው ለክልሉ ትምህርት ቤቶች የሚሰጡ ፈተናዎችንና የምስክር ወረቀቶችን ብቃት ያረጋግጣል፣

8. ለክልሉ የትምህርት ሥራ አስፈላጊ የሆኑ መጽሐፍትና ሌሎች የትምህርት መሣሪያዎች እንዲሟሉ ያደርጋል፣

9. የክልሉ የአንደኛና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶችን፣ የተቋቋሙትንና ወደፊት የሚቋቋሙትን ማሠልጠኛ ተቋማትንና መለስተኛ ኮሌጆችን ያደራጃል፣ ያስተባብራል፣

10. በክልሉ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በግል ለማቋቋም ለሚፈልጉ የሀገር ውስጥ ባለሀብቶችና ድርጅቶች ፍቃድ ይሰጣል፣ የብቃት ደረጃቸውንም ይቆጣጠራል፣

11. የክልሉን ትምህርት በጥራት ለማስፋፋት የሚያስችሉ ጥናቶችን ያካሂዳል፣ የትምህርትን ጥራት ለማስፋፋት የሚያስችሉ ፕሮጀክቶች አዘጋጅቶ በሥራ ላይ እንዲውሉ ያደርጋል፣ እንዲሁም በሀገር አቀፍ ደረጃ ለሚካሄዱ ጥናቶች አስፈላጊውን ድጋፍ ይሰጣል፣

12. ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ለአናሳ ብሔረሰቦች፣ ለሴቶች፣ ለህፃናትና ለጎልማሶች ለሚሰጡ የትምህርት አገልግሎቶች ልዩ ድጋፍ ይሰጣል፣

13. የክልሉ የትምህርት ፕሮግራሞች በመገናኛ ዘዴዎች እንዲደገፉ ያደርጋል፣

14. የትምህርት መረጃዎችን ይሰበስባል ያጠናቅራል፣ ለሚመለከታቸው አካላት ያስተላልፋል፣

15. ለትምህርት ሥራ አስፈላጊ የሆኑ የግንባታ ሥራዎችን ያቅዳል፣ ሲፈቀድም በሥራ ላይ ያውላል፣

16. ለተማሪዎች የሚሰጡ ልዩልዩ አገልግሎቶች የሚጠናከሩበትን ሥልት ይቀይሳል፣ ያስተባብራል፣

17. የትምህርት ፖሊሲውን መሠረት አድርጎ በመማር ማስተማሩ፣ በትምህርት አስተዳደር ተሳትፎውን በማጎልበት ሂደት እንዲሁም ለትምህርት ሥራ የሚያስፈልጉ የግንባታ ሥራዎች በስፋት የሚሳተፉበትን ሥልትና አደረጃጀት ይቀይሳል፣ ተግባራዊነቱንም ይከታተላል፣

## 15. የሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የጤና ቢሮ ሥልጣንና ተግባር

የሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የጤና ቢሮ የሚከተለው ሥልጣንና ተግባር ይኖረዋል፤

1. በክልሉ ውስጥ የጤና አገልግሎት እንዲስፋፋ ያደርጋል፤

2. የሀገሪቱን የጤና ፖሊሲ መሠረት በማድረግ ክልሉ ሕዝብ ጤና የሚጠበቅበትን ዕቅድና ፕሮግራም ያዘጋጃል፤ ሲፈቀድም በሥራ ላይ ያውላል፤

3. ስለ ሕዝብ ጤና አጠባበቅ የወጡ ህጎች፣ ደንቦችና መመሪያዎች በክልሉ ውስጥ እንዲከበሩ ያደርጋል፤

4. በየደረጃው የሚገኙ የጤና ተቋማትን፣ የጤና ምርምር ማዕከላትንና የማሰልጠኛ ተቋማትን ያደራጃል፤ ያስተዳድራል፤

5. በክልሉ ውስጥ ጥቅም ላይ የሚውሉ መድኃኒቶችና የህክምና መሣሪያዎችን ይመዘግባል፤ ይቆጣጠራል፤ በበቂ መጠንና በሚያስ ፈልጉበት ቦታ እንዲገኙ ያደርጋል

6. በሀገር ውስጥ ባለሀብቶችና ድርጅቶች ለሚቋቋሙ ጤና ጣቢያዎች፣ ክሊኒኮች፣ የምርመራ ድርጅቶችና መድኃኒት ቤቶች ፍቃድ ይሰጣል፤

7. በክልሉ ውስጥ በሕዝብ ጤና አግልግሎት ሥራ ላይ የተሰማሩ ባለሙያዎች የተወሰነውን ደረጃ ማሟላታቸውን ያረጋግጣል፤ ይቆጣጠራል፤ የጤናባለሙያዎች የሚሰለጥኑበትንም መንገድ ይቀይሳል፤

8. ዝቅተኛና መካከለኛ የጤና ባለሙያዎችን ያሰለጥናል፤

9. ፍቱንነታቸው የተረጋገጠ የባህል መድኃኒቶችና የህክምና ዘዴዎች ከዘመናዊ የህክምና ዘዴ ጋር ተዋህደው ሥራ ላይ እንዲውሉ ያደርጋል፤ ባለሙያዎችን ያደራጃል፤ ያበረታታል፤

10. የጤና ፖሊሲውን መሠረት አድርጎ ሕዝቡ በበሽታ መከላከል ላይ በስፋት የሚሳተፍበትንና ተላላፊ በሽታዎችን ለመከላከልና ለማጥፋት የሚያስችሉ ሥልቶችን ይቀይሳል፤ ተግባራዊ ነቱንም ይከታተላል፤

11. ለክልሉ ጤና አገልግሎት የሚያስፈልጉ የማንባታ ሥራዎችን ያቅዳል፤ ሲፈቀድም በተግባር ላይ መዋሉን ይከታተላል፤

12. የክልሉን ሕዝብ ለመጠበቅ የኳራንቲን ቁጥጥር ያደርጋል፤

13. ምግቦች ለሕዝቡ ጤና ተስማሚ መሆናቸውን ያረጋግጣል።

## 16. የሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት አደጋ መከላከል፣ ሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮ ሥልጣንና ተግባር

የሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የአደጋመከላከል እና የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮ የሚከተለው ሥልጣንና ተግባር ይኖረዋል፤

1. የሀገሪቱ የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ እና የአደጋ መከላከል ፖሊሲዎች በክልሉ ውስጥ ተግባራዊ እንዲሆኑ ያደርጋል፤

2. የሠራተኞችን ጉዳይ በሚመለከት የወጡ ህጎች፣ ደንቦችና መመሪያዎች በክልሉ ውስጥ መከበራቸውን ያረጋግጣል፤

3. የሠራተኞችን ደህንነትና ጤንነት ለመጠበቅ የወጡ የሥራ ሁኔታ ደረጃዎችና መከላከያ ዘዴዎች በሥራ ላይ መዋላቸውን ይቆጣጠራል፤

4. በክልሉ ደረጃ የሚቋቋሙትን የሠራተኛና አሠሪ ማህበራትን ይመዘግባል፤ አስፈላጊውን ድጋፍ ይሰጣል፤

5. የህብረት ስምምነት ድርድሮችና የሥራ ክርክሮች በህግ የተዘጋጀውን ሥርዓት ተከትለው በተቀላጠፈ ሁኔታ ፍፃሜ እንዲያገኙ አስፈላጊውን ጥረት ያደርጋል፤ እንዲሁም የህብረት ስምምነቶችን ይመዘግባል፤

6. አግባብ ካላቸው አካላት ጋር በመተባበር በክልሉ ስለተሰማራው የሰው ኃይል፣ ስለሙያ አመዳደብና አደጋ ሊመጣ የሚችልበትን ጥናት ያደርጋል፤

7. በክልሉ ውስጥ ሥራ ፈላጊዎችና ክፍት የሥራ መደቦች እንዲመዘገቡና ሥራና ሠራተኛ እንዲገናኙ የሚያስችል እርምጃ ይወስዳል፤

8. ስለክልሉ የሰው ኃይልና የሥራ ስምሪት ስለሠራተኞች ደህንነትና ጤንነት እንዲሁም ስለአሠሪና ሠራተኛን በሚመለከቱ ሌሎች

ጉዳዮች ላይ መረጃዎችን ያሰባስባል፣ ያጠናቅራል፣ እንዲሁም አስተያየቱን በማከል ለሚመለከታቸው አካላት ያስተላልፋል፣

9. የእርዳታ ግኝትና አስተዳደርን በሚመለከት የፌዴራሉ መንግሥት በሚያወጣው መመሪያ መሠረት ከእርዳታ ሰጭ ድርጅቶች ጋር ግንኙነት ያፈጥራል።

10. ከፌዴራል መንግሥት የአደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኮሚሽንእና ከሌሎች እርዳታ ሰጭ ድርጅቶች የሚገኘውንና ለክልሉ የተደለደለውን እርዳታ በትክክል ለተረጂዎች መድረሱን ያቆጣጠራል፣

11 በክልሉ ውስጥ አደጋ በተከሰተ ጊዜ የደረሰውን ጉዳት፣ መወሰድ የሚገባውን እርምጃና ለዚሁ የሚያስፈልገውን ድጋፍ በዝርዝር የሚያመለክት እቅድ ያዘጋጃል፣

12. ከፌዴራሉ መንግሥት የአደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኮሚሽን በክልሉ እንዲሠሩ የሚመደቡና በክልሉ ውስጥ የሚቋቋሙ መንግሥታዊ ያልሆኑ እርዳታ ሰጭ ድርጅቶችን ሥራ ያስተባብራል፣ ስለ ሥራቸው አፈፃፀም ምና ብቃት ለክልሉ መንግሥትና ለፌዴራል መንግሥት አደጋ መከላከልናዝግጁነት ኮሚሽን በየወቅቱ ሪፖርት ያደርጋል፣

13. የክልሉ ሴቶች በፖለቲካ፣ በኢኮኖሚ፣ በማህበራዊና በባህል ያላቸውን ተሳትፎ ለማጎልበት በፌዴራል መንግሥት የወጡ ፖሊሲዎች በክልሉ መንግሥትና በህብረተሰ ቡ ተግባራዊ እንዲሆኑ ያደርጋል፣

14 አግባብ ካላቸው አካላት ጋር በመተባበር ህፃናትና ወጣቶች መልካም አስተዳደግ እንዲያገኙ ለማድረግ የሚያስችሉ ዘዴዎች በክልሉ እንዲዘረጉ አስፈላጊውን ጥረት ያደርጋል፤ እንዲሁም የህፃናት መብትን በተመለከተ የዓለም አቀፍ ሰነዶች እና በሀገር አቀፍ የወጡት ህጎችና ደንቦች መከበራቸውን ይከታተላል፣

15. አግባብ ካላቸው አካላት ጋር በመተባበር በክልሉ ውስጥ የሚገኙ አረጋዊያንና የአካል ጉዳተኞችን ለመርዳትና መልሶ ለማቋቋም የሚያስችሉ ፕሮግራሞች ያዘጋጃል፣ ሲፈቀድም በሥራ ላይ ያውላል፣

16 የማህበራዊ ኑሮ ጠንቆች እንዲወገዱ የክልሉን ህብረተሰብ ያስተባብራል፣ አስፈላጊውንም ድጋፍ ይሰጣል፣

17. ለእርዳታ ፕሮግራሞች ማስፈፀሚያ የሚያስፈልጉና ልማት ነክ የሆኑ ፕሮጀክቶችን ዝግጅት ያስተባብራል፣ አፈፃፀማቸውንም ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን ይገመግማል፣

18 አግባብ ካላቸው አካላት ጋር በመተባበር የአደጋ ተጠቂዎችን መልሶ ያቋቁማል፣

19 አግባብ ካላቸው አካላት ጋር በመተባበር የቤተሰብ ደህንነት እንዲጠበቅ ለማድረግና የጋብቻ ሥርዓትን ለመንከባከብ የወጡ ፖሊሲዎችን ተግባራዊ ያደርጋል።

## 17. የሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ሲቪል ሰርቪስ ቢሮ ሥልጣልንና ተግባር

የሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የሲቪል ሰርቪስ ቢሮ የሚከተለው ሥልጣንና ተግባር ይኖረዋል፣

1 የመንግሥት ሠራተኞችን በሚመለከት በሀገሪቱ እና በክልሉ መንግሥት የወጡ ፖሊሲዎች፣ ህጎች፣ ደንቦችና መመሪያዎች የክልሉን መንግሥት ሲቪል ሰርቪስ ሠራተኞች በሚመለከት በሥራ ላይ መዋሉን ይቆጣጠራል፣

2. የፌዴራሉ መንግሥት የሚያወጣቸውን የሥራ መደቦች አመዳደብ መመሪያ ተከትሎ በክልሉ መንግሥት መሥሪያ ቤቶች ውስጥ የሚገኙ የሥራ መደቦችን ይመድባል፣

3. ለሲቪል ሰርቪስ ሠራተኞች የተፈቀደው የደሞዝ ስኬል፣ የልዩ ልዩ አበሎች ክፍያና ሌሎች የሥራ ሁኔታዎች የክልሉን መንግሥት የሲቪል ሰርቪስ ሠራተኞች በሚመለከት በሥራ ላይ እንዲውሉ ያደርጋል፣

4. የክልሉን መንግሥት ሲቪል ሰርቪስ ሠራተኞች አቀጣጠር፣ አመዳደብ፣ የደረጃ እድገት፣ የደሞዝ ጭማሪ፣ ዝውውር፣ ሥልጠናና የዲሲፕሊን አጠባበቅ በሲቪል ሰርቪስ ሠራተኞች ህጎች፣ ደንቦችና መመሪያዎች መሠረት እንዲፈፀም ያደርጋል፣ በክልሉ ተጨባጭ ሁኔታ ላይ ተመርኩዞ መመሪያ ያወጣል፣

5. የክልሉ መንግሥት ሲቪል ሰርቪስ ሠራተኞች ዝርዝር ይይዛል፣ እስታትስቲካዊ መረጃዎችን ያጠናክራል፣ ለፌዴራሉ የሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን ያስተላልፋል፣

6. የክልሉ መንግሥት ሲቪል ሰርቪስ ሠራተኞች ከጡረታ እድሜ ክልል በላይ አገልግሎታቸው እንዲራዘም በሚቀርቡ ጥያቄዎች ላይ የመጨረሻ ውሳኔ ይሰጣል፤

7. የክልሉ መንግሥት ሲቪል ሰርቪስ ሠራተኞች በችሎታ ማነስ ምክንያት ከሥራ ለማሰናበት በሚቀርቡ ጥያቄዎች ላይ የመጨረሻ ውሳኔ ይሰጣል፤

8.የክልሉ መንግሥት ሲቪል ሰርቪስ ሠራተኞች ህጉ በሚፈቅደው መሠረት በሚያቀርቡት [illegible]ባኝ ላይ የመጨረሻ ውሳኔ ይሰጣል፤

9. በፌዴራሉ ሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን ለሲቪል ሰርቪስ ሠራተኞች የሥራ ውጤት መመዘኛ የወጣው መመሪያ በክልሉ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ሥራ ላይ እንዲውል ከክልሉ ሁኔታ ጋር የተጣጣመ መመሪያ ያወጣል፤ በሥራ ላይ መዋሉንም ይቆጣጠራል፤

10.በክልሉ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች የሚፈጸሙት የጊዜያዊ ሠራተኞች ቅጥር በተመለከተ የወጣውን መመሪያ ተከትለው መፈፀማቸውን ይቆጣጠራል፤

11.የፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ህጎችን፣ ደንቦችና መመሪያዎችን በመተርጎም የሚያጋጥሙ ችግሮችን ለፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን ያስተላልፋል፤

12.[illegible]ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር የክልሉን መንግሥት መሥሪያ ቤቶች አደረጃጀትና የሰው ኃይል አጠቃቀም ገምግሞ የማሻሻያ ሃሣብ ያቀርባል፤ ሲፈቀድለትም ሥራና ሠራተኛ መገናኘቱን ያረጋግጣል።

## 18. የሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የፍትህ ቢሮ ሥልጣንና ተግባር

የሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የፍትህ ቢሮ የሚከተለው ሥልጣንና ተግባር ይኖረዋል፤

1.የህግ ጉዳዮችን በሚመለከት የክልሉ መንግሥት ዋና የሕግ አማካሪ ሆኖ ይሰራል፤

2. የክልሉ የህቃቤ ሕግ መሥሪያ ቤት የፖሊስ ኃይልና የማረሚያ ቤት አስተዳደርን በበላይነት ይመራል፤ ይቆጣጠራል፤

3.በክልሉ ሕገ-መንግሥት የተደነገጉትን የግለሰብ፣ የብሔር ብሔረሰቦች መብትና ነፃነቶች በክልሉ ውስጥ መከበራቸውን ያረጋግጣል፤

4. አግባብ ካላቸው አካላት ጋር በመተባበር በፌዴራሉ መንግሥት የወጡ ሕጎች በክልሉ መንግሥት የሥራ ቋንቋ እንዲተረጎሙ ያደርጋል፤

5. በክልሉ ፍርድ ቤቶች ሥልጣን ሥር በሚወድቅ የወንጀል ጉዳዮች የክልሉን መንግሥት በመወከል ይከራከራል፤

6. የሕዝቡን እንዲሁም የክልሉን መንግሥት መብትና ጥቅም ለማስከበር አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው በፌዴራልና በክልሉ ፍርድ ቤቶች እንዲሁም በማንኛውም በዳኝነት ሰሚ አካል ወይም የሽምግልና ጉባዔ ክስ ይመሰርታል፤ ክስ እንዲመሠረት ያደርጋል ወይም ጣልቃ በመግባት ይከራከራል፤ እንደነገሩ ሁኔታ ተከላካይ በመሆን ይቀርባል፤

7.የወንጀል ምርመራ ክፍሎች ሥራቸውን በሕግ መሠረት ማከናወናቸውን ያረጋግጣል፤ ወንጀል ተፈጽሟል ብሎ ሲያምን ምርመራ እንዲደረግ ያዛል፤ በቂ ምክንያት ሲኖር የተጀመረ ምርመራ እንዲቆም ወይም ተጨማሪ ምርመራ እንዲከናወን ያደርጋል፤ እንዲሁም አንድ የወንጀል ጉዳይ ከአንድ የምርመራ ክፍል ወደ ሌላ የምርመራ ክፍል ወይም ከአንድ መርማሪ ወደ ሌላ መርማሪ እንዲዛወር ያደርጋል ወይም እራሱ ይመረምራል፤

8. በሕግ የተሰጡትን ሥልጣንና ተግባር በሚመለከት የሚቀርቡለትን አቤቱታዎች በመመርመር ተገቢውን ሕጋዊ ውሳኔ ወይም ትዕዛዝ ወይም መመሪያ ይሰጣል፤

9.የወንጀል መንሻዎችና የመከላከያ ዘዴዎችን ያጠናል፤ ወንጀል የሚቀንስበትን ስልት ይቀይሳል፤

10.የወንጀል ድርጊት ምሥክሮች እንደ አስፈላጊነቱ ተገቢውን የሕግ ጥበቃ እንዲያገኙ ያደርጋል፤

11. አግባብ ካላቸው አካላት ጋር በመተባበር በክልሉ የሕግ ሥልጠና ፕሮግራም ያዘጋጃል፤

12.በክልሉ መንግሥትና የአስፈፃሚ አካላት ጥያቄ ሲቀርብለት የሕግ ረቂቆችን በማዘጋጀት ይረዳል፤

13. በክልሉ መንግሥት ወይም አስፈፃሚ አካላት ላይ የሚቀርቡትን የፍትሀ ብሔር ክሶችና ጥያቄዎችን እያያዘ ይከታተላል፤ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ሪፖርት እንዲቀርብለት ያደርጋል፤ ለዚሁም ብቃት ያለውየሰውኃይል መመደቡን ያረጋግጣል፤

14. ስለጥብቅና ሥራ ፍቃድ አሰጣጥ በሚወጣው ደንብና መመሪያ መሠረት በክልሉ ፍርድ ቤቶች መከራከር ለሚችሉ ጠበቆች ፍቃድ ይሰጣል፤ ይቆጣጠራል፤

15. የክልሉን ሕብረተሰብ ንቃተሕግ ለማዳበር በተለያዩ ዘዴዎች የሕግ ትምህርት ይሰጣል፤

16. የክልሉ መንግሥት ሕጎችን በበላይነት ይይዛል፤ የኮድፊከሽንና ሕጎችን የማጠቃለል ሥራ ያካሂዳል፤ የክልሉ መንግሥት ሕጎችን በማሰባሰብ በተወሰነ ጊዜ እንዲጠቃለሉ ያደርጋል፤

17. ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር የሚቋቋሙ አትራፊ ያልሆኑ ማህበራትን ይመዘግባል።

19. <u>የሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ባህልና ስፖርት ቢሮ ሥልጣንና ተግባር</u>

የሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ባህልና ስፖርት ቢሮ የሚከተለው ሥልጣንና ተግባር ይኖረዋል፤

1. ባህል፤ ኪነ-ጥበብ፤ አካል ማጎልመሻና ስፖርት በክልሉ እንዲዳብርና እንዲስፋፋ ያደርጋል፤ እንዲሁም የሥነ-ጥበብ የፈጠራ ችሎታ እንዲዳብር ያበረታታል፤

2. በፌዴራሉ መንግሥት የሚመለከታቸው ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቶች የሚያወጡአቸውን መመሪያዎች ተከትሎ በክልሉየሚገኙ ታሪካዊ ቅርሶች እንዲፈለጉ፤ እንዲጠኑ፤ እንዲጠበቁ፤ እንዲታደሱ፤ ጥቅምላይ እንዲውሉ ያደርጋል፤ ቅርሶችንና በመጥፋት ላይ ያሉትን የክልሉን ባህሎች ከዝርዝር መግለጫ ጋር ይመዘግባል፤

3. በክልሉ ውስጥ በማንኛውም ሰው፣ ማህበር፣ የኃይማኖት ድርጅት ወይም ተቋም እጅ የሚገኙ ቅርሶች በሚገባ እንዲያዙ ድጋፍ ይሰጣል፤

4. በክልሉ ውስጥ የህዝብ ቤተመጽሐፍት፤ ቤተ መዛግብት፤ አብያተ መዘክሮች ሙዚየሞች እንዲስፋፉ ያደርጋል፤

5. ሲኒማ ቤቶችና ቲያትር ቤቶች በክልሉ ውስጥ እንዲስፋፉ ያደርጋል፤

6. የክልሉ ሕዝብ ታሪክና ባህል ተመዝግቦ እንዲያዝ፤ ቋንቋው እንዲጠናና ሥነ-ጽሁፍ እንዲዳብርና እንዲስፋፋ ያደርጋል፤

7. በክልሉ ውስጥ ለሚቋቋሙ የስፖርት ማህበራት ፍቃድ ይሰጣል፤ ፕሮግራሞቻቸውንም ያስተባብራል፤ ይቆጣጠራል፤

8. በክልሉ ውስጥ በክልል ደረጃ ውድድሮችን ያዘጋጃል፤ እንዲዘጋጁም ፍቃድ ይሰጣል፤

9. በክልል ደረጃ የሚዘጋጁትን የስፖርት ውድድሮች በሚመለከት በስፖርት ማህበሮች መካከል የሚነሳውን ክርክር ይዳኛል፤

10. በክልሉ ውስጥ ባህላዊ ስፖርቶች የበለጠ እንዲታወቁ፤ እንዲሻሻሉና እንዲያድጉ ያደርጋል፤

11. በክልሉ ውስጥ የስፖርት ማዘውተሪያ ሥፍራዎችን ያዘጋጃል፤ እንዲዘጋጁም ያበረታታል፤

12. የክልሉ ስፖርት ምክር ቤቶችን እና የባህል መማክርት ጉባዔን ያቋቁማል፤

13. የክልሉ ስፖርት ማህበራት የሚያገኙት ገቢ ለዓላማቸው ማስፈፀሚያ ብቻ መዋሉን ለማረጋገጥ ሂሣባቸውን ይመረምራል፤

14. የሐረሪ ሕዝብ ታሪክና ቋንቋ እንዲጠና እንዲዳብር እንዲሁም ታሪካዊና ባህላዊ ቅርሶች እንዲጠበቁና ጥቅም ላይ እንዲዉሉ ያደርጋል፤

15. ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር የስፖርት ትጥቅና መሣሪያዎች እንዲሁም የሥነ-ጥበብ መሣሪያዎች የሚገኙበትን ሁኔታዎች ያመቻቻል፤

16. ከክልሉ ጤና ቢሮ ጋር በመተባበር ስፖርታዊ ሕክምናን ያዘጋጃል።

## ምዕራፍ ሦስት

## የሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የጽህፈት ቤቶች ሥልጣንና ተግባር

## ክፍል አንድ

## የጽህፈት ቤቶችና

## የጽሕፈት ቤት ኃላፊዎች የወል ሥልጣንና ተግባር

### 20. የወል ሥልጣንና ተግባር

...ሀ አዋጅ በአንቀጽ አምስት የተመለከቱ የቢሮዎች የወል ሥልጣንና ተግባር በዚህ አዋጅ በአንቀጽ አራት መሠረት ለተቋቋሙት ጽሕፈት ቤቶችም ተፈጻሚ ይሆናል።

### 21. የጽሕፈት ቤቶች ኃላፊዎች ሥልጣንና ተጠሪነት

በዚህ አዋጅ አንቀጽ ስድስት እና ሰባት ስለ ቢሮ ኃላፊዎች የተደነገጉት በዚህ አዋጅ አንቀጽ አራት መሰረት ለተቋቋሙት ጽሕፈት ቤቶች ኃላፊዎችም ተፈጻሚዎች ናቸው።

## ክፍል ሁለት

## የሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የጽህፈት ቤቶች

## ዝርዝር ሥልጣንና ተግባር

### 22. የሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የሴቶች ጉዳይ ዘርፍ ሥልጣንና ተግባር

1. በክልል ደረጃ የሴቶችን ጉዳይ ያስተባብራል፣ ያቀናጃል፣ ይከታተላል፤

2. የሴቶችን ጉዳይ በሚመለከት በፌዴራል መንግሥቱና በክልሉ መንግሥት የወጡ ፖሊሲዎች፣ ሕጎችና መመሪያዎች በክልሉ ውስጥ በሥራ ላይ መዋላቸውን ይከታተላል፤

3. የክልሉ ሴቶች መሠረታዊ ችግሮች ተለይተው እንዲታወቁ መፍትሄ እንዲያገኙ ያደርጋል፤

4. የክልሉ ሴቶች ከጸታ ተፅዕኖ ውጪ በክልሉ በሚካሄደው የልማት እንቅስቃሴዎች በስፋት እንዲሳተፉ ያደርጋል፤

5. በፌዴራሉ ሕገ-መንግሥትና በክልሉ ሕገ-መንግሥት የተረጋገጡት የሴቶች መብቶች ተግባራዊ መሆናቸውን ይከታተላል፣ ያረጋግጣል፤

6. መንግሥታዊና መንግሥታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች ታቅደው የሚካሄዱ ፕሮጀክቶችና ፕሮግራሞች የክልሉን ሴቶች ሊጠቅሙ የሚችሉበትን ሁኔታ በማጥናት ሐሳብ ያቀርባል፣ ተግባራዊ መሆኑንም ይከታተላል፤

7. በክልሉ የመንግሥት አካላት የሚካሄዱ የልማት እንቅስቃሴዎችና የሚወጡ ዕቅዶች የክልሉን ሴቶች ተሳትፎና አቅም ያካተተ መሆኑን ያረጋግጣል።

### 23. የሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የኢንቬስትመንት ጽ/ቤት ሥልጣንና ተግባር

የሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የኢንቬስትመንት ጽ/ቤት የሚከተለው ሥልጣንና ተግባር ይኖረዋል፤

1. ስለኢንቬስትመንት የወጡ ፖሊሲዎችና ሕጎች በክልሉ ውስጥ በትክክል መፈፀማቸውን ያረጋግጣል፣ ይቆጣጠራል፤

2. የሚቀርብለትን የኢንቬስትመንት ማመልከቻዎችን መርምሮ ኢንቬስትመንትን በሚመለከት በወጣው ሕግ የተደነገጉት መስፈርቶች ተሟልተው ሲገኙ የኢንቬስትመንት ፍቃድ ይሰጣል፣ በዚህም መስክ አስፈላጊውን ገቢ ይሰበስባል፤ የሰበሰበውንም ገቢ ያስተዳድራል፤

3. ስለ ኢንቬስትመንት የወጡ ሕጎች ላይ የተደነገጉት ጥፋቶች ሲፈፀሙ ወይም ለኢንቬስትመንት እንቅስቃሴ ጎጂ የሆኑ ጥፋቶች ሲፈፀሙ እንደአስፈላጊነቱ የሰጠውን ፍቃድ ይሰርዛል፤ ጥፋቱን የፈፀሙ ሰዎችም በሕግ እንዲጠየቁ ያደርጋል፤

4. የኢንቬስትመንት ፍቃድ የተሰጣቸው ባለሀብቶች የሚያቀርቧቸው የማበረታቻ ጥያቄዎች ስለኢንቬስትመንት በወጣው ሕግ የተደነገጉትን አሟልተውየቀረቡ መሆናቸውን አረጋግጦ ተገቢውን ውሣኔ ይሰጣል፤

5. በክልሉ ውስጥ የሚገኘውን የሀብት ክምችትና የኢንቬስትመንት ዕድል መረጃዎችን ያሰባስባል፤ ያጠናቅራል፤ የሰበሰበውንም መረጃዎች ለባለሀብቶች ያሰራጫል፤ እንዲሁም ተጨባጭ

የኢንቬስትመንት ፕሮጀክቶችን ለባለሀብቶች ያስተዋውቃል፣

6.በባለሀብቶችና ጉዳዩ በሚመለከታቸው የክልሉ መንግሥት አካላት መካከል የኢንቬስትመንት ተግባራትን ያስተባብራል፣ ይቆጣጠራል፣

7. በክልሉ ውስጥ የሚደረግ የኢንቬስትመንት እንቅስቃሴን አስመልክቶ ተዝሊውን አገልግሎት ይሰጣል፣

8. ስለክልሉ የሀብት ክምችት፣ የኢንቬስትመንት ዕቅድና እንቅስቃሴ መረጃዎችን በማጠናቀርና ሪፖርት በማዘጋጀት ለፌዴራሉ የኢንቨስትመንት ጽህፈት ቤት ያስተላልፋል።

## 24. የሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የሥነ-ሕዝብ ጽ/ቤት ሥልጣንና ተግባር

የሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የሥነ-ሕዝብ ጽ/ቤት የሚከተለው ሥልጣንና ተግባር ይኖረዋል፣

1. የክልሉ ሥነ-ሕዝብ ጉዳይ ጽህፈት ቤት የክልሉ ሥነሕዝብ ጉዳይ ምክር ቤት ጽህፈት ቤት ሆኖ ያገለግላል፣

2. በሥነ-ሕዝብ መስክ የሥራ ፕሮግራም ያዘጋጃል፣ ይመራል፣

3. በተለያዩ የሥነ-ሕዝብና የልማት ዘርፎች ላይ የተሰማሩትን የክልሉ መንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ መሥሪያ ቤቶች እንቅስቃሴን ያስተባብራል፣ መርሀ-ግብሮችን ይከታተላል፣ ይገመግማል፣

5. በተለያዩየክልሉ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶችና ድርጅቶች የሚካሄድ የሥነ-ሕዝብ መርሀ ግብሮችን በሀገሪቱ የሥነ-ሕዝብ ፖሊሲና የክልሉ የሥነ-ሕዝብ ጉዳይ ምክር ቤት በሚያወጣው መመሪያዎች መሰረት መፈፀማ ቸውን ያረጋግጣል፣

6.በክልሉ የሥነ-ሕዝብ ልማት ላይ የሚያተኩሩ ፖሊሲ ነክ ምርምሮችን ያካሂዳል፣ ያስፋፋል፣

7. የሥነ-ሕዝብ ፖሊሲን በክልሉ በሥራ ላይ ለማዋል የሚያስፈልጉ ልዩ ልዩ የሥራ ግብረ ኃይሎችና የቴክኒክ ኮሚቴዎችን ያቋቁማል፣

8. በክልሉ የመዋቅር ተዋረድ መሠረት የሥነ-ሕዝብ ጉዳይ ጽህፈት ቤት አስፈላጊውን የሥነ-ሕዝብ መረጃዎች፣ የምክርና የቴክኒክ ድጋፍ ይሰጣል፣

9. በክልል ደረጃ ልዩልዩ የሥነ-ሕዝብ ፕሮግራሞችን ያዘጋጃል፣ ያካሂዳል፣

10. የሥነ-ሕዝብ ልማት መረጃዎችን በማሰባሰብ ተግባር ይሳተፋል፣

11.በሥነ-ሕዝብ ኢንፎርሜሽን ትምህርት መገናኛ አማካ ይነት የክልሉን ህብረተሰብ ተሳትፎ ያጎለብታል።

## ምዕራፍ አራት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### 25 መብትና ግዴታዎችን ስለማስተላለፍ፣

ይህ አዋጅ ከመፅናቱ በፊት በክልሉ ተቋቁመው የነበሩ ቢሮዎች ወይም መሥሪያ ቤቶች ይህ አዋጅ ከፀናበት ጊዜ ጀምሮ ከሌሎች ቢሮዎች እንዲዋሃዱ የተደረጉ ቢሮዎች መብትና ግዴታ ወደ ተዋሀዱበት ቢሮዎች ተላልፏል።

### 26. ተፈፃሚነት የሌላቸው ሕጎች

ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረን ማንኛውም ሌላ የክልሉ ሕግ ይህ አዋጅ በሚመለከታቸው ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚ አይሆንም።

### 27. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ በሐረር ነጋሪ ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ጊዜ ጀምሮ የፀና ይሆናል።

ሐረር መጋቢት 5 ቀን 1988

አብዱላሂ እድሪስ

የሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ

መንግሥት ፕሬዚዳንት